# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 32     መስከረም 15 ቀን 2015 (25-09-2022)

የዛሬውን ቅንብራችንን ከሌላው ጊዜ ለዬት የሚያደርገው ከመደበኛው የሳምንቱ ክስተት ጋር ተያይዞ በመጣው የክህደት ተግባር ላይ የምናቀርበው ትንታኔን ያካተተ በመሆኑ ነው።ከዚያ በፊት ግን የተከናወኑትን ዋና ዋና ጉዳዮች ገረፍ ገረፍ ለማድረግ እንወዳለን።

መቋጫ ያላገኘው የሰሜኑ ጦርነት አሁንም እንደቀጠለ ነው።ከፕሮፓጋንዳ ጫጫታ በቀር የመሸነፍና የማሸነፍ ውጤት አልታዬም፤ሕዝቡም ከሁለቱም ሃይሎች የመከራ አጣብቂኝ አልወጣም።።አንዱ ጧት የያዘውን ቦታ ማታ ላይ መልቀቁንና በሌላው መሸነፉን የሚነገረው ወሬ ከጆሮ ሳይወጣ እንደገና በሌላው ቦታ በተደረገ ጦርነት  መነጣጠቁ ይነገራል፣ጦርነቱ  የመንግሥትና የወያኔ ደጋፊ የዜና ተቋማትና ጋዜጠኞች የእንጀራ ማዕድ ማወራረጃ የውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ጨዋታ እዬሆነ የብዙ ዜጎችን ህይወት ከመቅጠፉና ከማናጋቱ በተረፈ ያመጣው ለውጥ የለም።በፊትለፊት በጦርነት ላይ የተሳተፉ መሆናቸውንና በድል ላይ ድል መመዝገባቸውን እያናፈሱ በስከጀርባ ለመደራደር እላይ እታች እያሉ መሆናቸውን ሳይደብቁና ሳያፍሩ ያስተጋባሉ።ለሁለቱም እንቅፋት የሆነባቸው የአማራው በኢትዮጵያ አንድነት፣እንዲሁም  በወልቃይትና በራያ ላይ ያለው የማይናወጥ አቋሙ ነው።ያንንም ለማኮላሸት ያልሞከሩት የለም ፤አሁንም በመሞከር ላይ ናቸው።

ከምዕራባውያን ጋር በስከጀርባ የሚያደርጉትም የስምምነት መዳረሻ የአገር ወዳዶቹን  ኢትዮጵያውያን በተለይም የአማራውን ቅስም ለመስበር በሚያስችለው ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው።ኦሮሚያ በሚባለው በኦነግ ኦሕዴድ በሚተዳደረው ክልል ውስጥ አማራው ሲጨፈጨፍ ብአዴን የተባለውን በአማራው ስም በመንግሥት ተብዬው ስብስብ ውስጥ የተሰገሰገውን አሽከር ድርጅት ደንታ አልሰጠውም፣ይባስ ብሎም አማራውን ማሳደድ ታማኝነቱን የሚገልጽበት ሙያ አድርጎታል።ምዕራባውያኑም ለሚፈሰው የንጹሃን ደም ትኩረት አልሰጡትም፤የሚያሳስባቸው ለነሱ ተላላኪ የሆነ ቡድን በሥልጣን ላይ የመቀመጡ እንጂ የኢትዮጵያ አንድነትና የሕዝቡ ሰላማዊ ኑሮ አይደለም።አማራውን መጨረስና አቅመቢስ መሆን ለኦነግ ኦሕዴድም ሆነ ለህወሃት አገር የማፈራረስ ፕሮጀክት አንዱና ዋናው አካል ስለሆነ ይረባረቡበታል፤ጦርነቱንም የብርና የድጋፍ መሰብሰቢያ ስላደረጉት እንዲቆም አይፈልጉም። ለሁለቱም  እራስ ምታት የሆነባቸው የአማራው መነሳሳት ነው።ያንን ለማጥፋት ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም።አሁንም ቀጥለውበታል።

በአገራችን የሚካሄደውን አለመረጋጋትና የእርስ በርስ ጦርነት ምዕራባውያን  የዲፕሎማሲ፣  የፖለቲካና የፕሮፓጋንዳ ጡንቻ ማሳያ አድርገውታል።በነሱ ፍላጎት ልክ ያገሪቱ እጣ ፈንታ እንዲወሰን ከአንዱ ጋር በመጣበቅ የሚያደርጉት አሻጥር ገጦ የታዬበት ጊዜ ቢኖር አሁን ነው።ፍላጎታቸው በኢትዮጵያ ከተሳካላቸው ለሌላው የአፍሪካ አገር የመቀጣጫ መልእክት የሚያስተላልፉበት መንገድ ይሆናል።ለእኛ ለኢትዮጵያኑ የሚበጀውና የሚያዋጣው ብቸኛው መፍትሔ  ለዚህ መከራና ችግር የዳረጉንን የህወሃትና የኦነግ ኦህዴድ ብልጽግና ቡድኖች ማሶገድ ብቻ ነው።እነዚህ እኩይ የጎሳ ስብስቦች የዘረጉት ስርዓት ካልተወገደ በቀር የውጭ ሃይሎች የሚገቡበት ቀዳዳ አይደፈንም፤ በአገራችን ሰላምና አንድነት አይሰፍንም። እነዚህ እኩይ ቡድኖች እስካሉ ድረስ የእርስ በርሳችን እልቂት ይቀጥላል፣ከእኛም አልፎ ለትውልድ ተሻጋሪ የሆነ ቂምና ጥላቻ እንዲኖር ያደርጋል ። ስለሆነም የትግራይና ሌላው ጎሳ ተወላጅ ወደ ልቦናው ተመልሶ በስሙ ሥልጣን ላይ ተቀምጠው ለጥፋት የሚጋልቡትን የወያኔንና የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግናን ቡድኖች ከጫንቃው ላይ አውርዶ መጣልና ተገቢ ቅጣታቸውን መስጠት ይኖርበታል የሚለውን  ጥሪያችንን አሁንም እንደግማለን።

በሰሞኑም  የወሊጋው የአማራ ተወላጅ ጭፍጨፋ እንደቀጠለ ነው፤እዬከፋ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም። የድረሱልን ጥሪ ቢያስተጋቡም የደረሰላቸው የለም።የክልሉ አስተዳደርና ልዩሃይል ከገዳዮቹ ጋር ተባባሪ በመሆን የወንጀሉ ተካፋነቱን በግልጽ አሳይቷል። በአዲስ አበባ ከተማም የተረኛው የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ድፍረት እየጨመረ እንጂ እዬቀነሰ አልመጣም።ኂላቀርነት በወለደው እብሪት የሚከናወነው የማን አለብኝ ሥራ በሰፊው ቀጥሏል። ባለፉት ዘገባዎቻችን ደግመን ደጋግመን እንደገለጽነው በዚህኛውም ሳምንት በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ የኦነግን ባንዲራ የመስቀልና ጥላቻና የውሸት ትrkeት በማስተጋባት  ለእርስ በርስ ግጭትና ጦርነት የሚቀሰቅስ መዝሙር ለማዘመር በተደረገው ሙከራ ተማሪዎች፣መምህራንና ወላጆች ተቃውሟቸውን ሲገልጹ ያዬንበት ሰሞን ነው።ይህ በመንግሥት እውቅናና ትዕዛዝ በከተማዋ አስተዳደር አስፈጻሚነት የሚካኼደው  ሕዝብ አጫራሽ አገር አፍራሽ የሆነ እርምጃ በጊዜው ካልተቀጨ ይዞት የሚመጣው ጣጣ ቀላል አይሆንም።

አገራችን በሁሉም አቅጣጫ ከተዘፈቀችበት ቀውስ ውስጥ ሊያወጣት የሚችል ሕዝባዊ እንቅስasy አልታዬም። በውጭ ጠላቶች የሚታገዝ ሃይልና ቡድን እንደ አሸን በፈሉበት፣ የእርስ በርስ ጦርነት የብዙዎችን ህይወት ሲቀጥፍ የሕዝቡ ትኩረት  ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ለችግርና ለድህነት ባጋለጠው በኑሮ ውድነቱ ላይ ነው።የእለት ጉርስ ብርቅ የሆነበት የከተማዋ ነዋሪ ሕዝብ ለመብቱና ለአገሩ አንድነት የተጨነቀለት አይመስልም።ትልቁ ሃሳብና ጭንቀቱ ሆዱን ሞልቶ ማደሩ ሆኗል።ብዙሃኑ አሁንም በዝምታ ድባብ ውስጥ ላይ ነው።ፍርሃት ይሁን በሥርዓቱ የመርካት ሊታወቅ አልቻለም።እረክቶ ነው እንዳይባል ኑሮ ተወደደብኝ እያለ እሮሮ ያሰማል።እንደው ግራ ገብቶት ግራ የሚያጋባ ሕዝብ ሆኖብናል።ለመብቱ የሚጮሁትን አሳልፎ ሲሰጥ ስናይም ፣የከህደት ተሸካሚው ሕዝቡ ነው ለማለት እንደፍራለን።ከሞቀ ቤታቸው፣ከቤተሰባቸው፣ከሕጻን ልጆቻቸ ይልቅ የወገናቸውና ያገራቸው ጉዳይ አሳስቧቸው ግንባር ቀደም ለመሆን የተሰለፉት በእስርቤት ሲማቅቁ በዝምታ የሚያይ፣ለእኔ ነው ብሎ የማይጮህ፣ሌላው ቀርቶ ለቤተሰቦቻቸው የማያዝን፣ስንቅ ለማቀበል የማይደፍር ሕዝብ እውነትም ከሃዲ ነው ለማለት ያስደፍራል።ጀግና ልጆቹን ከመከተል ይልቅ ወደሞት እዬሸኘ በስማቸው መነገድና በየሚዳው መጨፈር ፣የቆመ ወቃሽ የሞተ አወዳሽ መሆኑ እልም ያለ ክህደት ነው።

በየእምነቱ አስተምሮ ሌላውን እንደራስህ ውደድ የሚለውን ቃል ደጋግሞ ቢሰማውም አንድ ጊዜም እንኳን ቢሆን በተግባር ለመተርጎም የሚሞክረው በጣም ጥቂቱ ነው።አንዳንዶቹ የእምነት አባቶችም ደፍረው  ምእመናኑን ደፋር አላደረጉትም። ይባስ ብለው ቀጣይ መከራና ግፍ እንዲቀበል “ግራህን ሲመታህ ቀኝህን ስጠው” የሚል የአጎብዳጅነት ትምህርት እየጋቱት ነው።እምቢ ያለውንም በእርቅና ሽምግልና ስም ገብሮ እንዲያድር እየገዘቱ፣ባማላጅነት እያስገደዱት ወደ መታረጃው እንዲነዳ ካራጁ ሥርዓት ጋር ተባባሪ ሆነዋል።ሌላው ቀርቶ በራሳቸው መንበር ፣በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ የሚደርሰውን ድፍረትና የማጥቃት ዘመቻ በድፍረት ሊቋቋሙት አልቻሉም፣የጴጥሮስን ሳይሆን የይሁዳን መንገድ የመረጡ መስለዋል።

ሕዝቡም ሆነ የእምነት አባቶች ለምን እንዲህ ሆኑ ብለን ስንጠይቅ  በፍርሃት በመቀፍደድ፣ለብሶቱ መፍትሔ የሚፈልግለት ሁነኛ መሪ ድርጅት ባለመኖሩ፣ድርጅቶች ቢኖሩም እምነት የማይጣልባቸውና በሥልጣን የሚሸጡ ከሃዲዎች መሆናቸውና ያንንም ተደጋግሞም ስላዩ፣በግለሰቦችም በኩል ለግል ጥቅም የሚሽቀዳደሙና ሌላውን አሳልፈው የሚሰጡ ከሃዲዎችና አድርባዮች በመብዛታቸው ተስፋ በመቁረጡ ነው ከሚለው ድምዳሜ ላይ ደርሰናል።

የክህደትን ነገር ካነሳን አይቀር የሰሞኑን አዬር ውጦት ወደሰነበተው ወደ ፋኖ ዘመነ ካሴ መታሰር ፊታችንን እንድናዞር ሁኔታው ያስገድደናል።የፋኖ ዘመነ ካሴ መታሰር ከተፈጸመበት የክህደት ስራ ጋር የተሳሰረ መሆኑን የሚገልጹ ብዙ ማብራሪያዎች በአሽሙርም ይሁን በሃሜት ለመስማት ችለናል።እኛም

የፋኖ ዘመነ ካሴን መያዝ ስንሰማ ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ተሰምቶናል፣ትግሉ አስመርሮት ወይም ተስፋ ቆርጦ እራሱ በፈቃዱ እጁን ሰጠ?ሳያስበው ተከቦ ተያዘ?ሽማግሌዎች አባብለው ለድርድር እንዲቀርብ ተደርጎ ከደው አሲያዙት? እነዚህ በአይምሯችን እዬተሽከረከሩ ባለበት ሁኔታ በመንግሥት በኩል በተሰጠው መግለጫ ደግሞ በአንድ ደሳሳ ቤት ውስጥ እንደተራ ሌባ ተደብቆ ያዝነው ሲባል ፣ከአነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መንግሥት ከዚህ የተለዬ መግለጫ ባይጠበቅም ድርጊቱን በጽሞና እንድንመረምረው አድርጎናል።

እኛ በፋኖ ዘመነ ካሴም ሆነ በሌሎቹ የፋኖ ቡድን መሪዎች ላይ ከሠሩትና ለመሥራት ከተነሱበት ዓላማ አንጻር ፣የሰዎቹንም ንቃተ ሕሊና ከግምት ውስጥ በማስገባት ካለን ግንዛቤ ስንነሳ ከትግሉ ሸብረክ ይላሉ ወይም በሥርዓቱ ላይ እምነት አድሮባቸው ለመደራደር ካለምንም ቅድመ-ሁኔታ ይወስናሉ የሚል እምነት የለንም። ሆኖም ግን ዘመነም ሆነ ሌላው የሰው ልጅ ነውና ስህተት ሊሠራ አይችልም የሚል ግትር አቋም የለንም።በተለይም ሁኔታውን ተከትሎ ብቅ ብቅ ያሉ ፍንጮችን ስንከታተል በአነግ ኦሕዴድ ብልጽግና አሸከር በሆነው የክልሉ አመራር የተያዙ ከአሥር ሽህ በላይ የሚሆኑ የአማራ ፋኖዎችን ለማስለቀቅና ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት በቀረበ ሃሳብ ምክንያት ለመደራደር በመጣበት ጊዜ የተፈጸመ ክህደት ነው የሚለው ቀልባችንን ሊስበው ችሏል። ይህ ማለት ግን ትክክልና ተገቢ ነው ማለታችን አይደለም።ሲጀመር ጠላት ጋር ድርድር የሚሉ ነገር አይታሰብም።ድርድር ከታሰበ ጫካ መግባትን ምን አመጣው? ጫካ መግባትና መሣሪያ ማንሳት እኮ የሰላም በሩ ጥርቅም ተደርጎ ሲዘጋና ችግርን በሰላማው ድርድር የመፍታቱ መንገድ ሲጠፋ ነው።በተለይም ከተቻለ በህይወት ካልተቻለም ተገሎ አስከሬኑ ይምጣ ብሎ ከወሰነ አካል ጋር እደራደራለሁ ብሎ ማሰብ የማይዋጥልን ውሳኔ ነው።የዚህ አይነቱ ጠላትን በቅጡ ያለማወቅ ድክመት የጎራ መደበላለቅንን ያስከትላል፣ ዓላማን ያናጋል የምንለውም ለዚያ ነው።ድርድር ቢታሰብ እንኳ ተደራዳሪ ቡድን ይላካል እንጂ ብልጽግና ዋና ጠላቴ ነው፣እገለዋለሁ ያለው ዘመነ ካሴ መቅረብ አልነበረበትም።

ስህተትን አውጥቶ መናገር ማጋለጥ ሳይሆን ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ይረዳል።እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ መሰሉ ስህተት ባለፉት ጊዜያቶች ተደጋግሟል።አሁንም ሲደገም ማዬቱ ምክንያቱን በጥልቀትና በድፍረት እንድናዬው አስገድዶናል።በወደቀ ዛፍ ላይ ምሳር ይበዛበታል በሚል የማምለጫ አባባል ቡድናዊ ለመሆንና ስህተትን ለመደበቅ አንሻም።በሕዝብ ላይ የተደረገ ሸፍጥ ከመሰለን ያንን ከማውገዝና ከማጋለጥ አንመለስም። ድክመት ካለም ተወግዶ ይበልጥ ለመጠናከር መነሻውን ማወቅና ምንጩን ማድረቅ የደፋርና የእውነተኛ ታጋዮች ግዴታ ነው።ስህተትን በቡድናዊነት መሸፋፈን አገርና ሕዝብ ይጎዳል።በሽታውን የደበቀ መድሃኒት አይገኝለትም ይባላልና እኛ ጋር መደባበቅ የለም። ትክክሉን ትክክል፣ስህተቱንም ስህተት ከማለት አንመለስም።ከሳምንታት በፊት በነበረን ስርጭት ላይም “ቃል” የሚለው የግጥም መልእክታችን ይህንኑ አቋማችንን የሚገልጽ ነበር።

ሌላው ቢቀር ከድርድር በፊት የታሠሩትን ማስለቀቅ አንዱ ቅድመ ሁኔታ መሆን በተገባ ነበር። የታሰሩትን ለማስፈታት ሲል ያደረገው መቀራረብ ነው የሚሉም አልጠፉም።ይህም ቢሆን ተደራድሮ ያላሳሰራቸውን ተደራድሬ አስፈታለሁ ብሎ መነሳት በራሱ ስህተት ነው። ለፋኖ መነሳት ምክንያት የሆነው በኢሕአዴግ-ብልጽግና አገዛዝ ለ32 ዓመታት የቆዬው በአማራው ላይ የሚፈጸመው ጭፍጨፋና በደል፣የአገር አንድነትና ልዑላዊነት ጥያቄ እንዴት በሰላማዊ መንገድ ሊወገድ ይችላል ተብሎ ይታሰባል?ስለሰላምስ ብዙ ተሞክሮ አልነበረም ወይ? ለወንጀሉ ሁሉ ተጠያቂው ማነው?በወንጀለኛው ላይ የሚወሰድበትስ እርምጃ ምን መሆን አለበት? በሚለው ዙሪያ ጥልቅ ውይይት ተደርጎ አቋም መውሰድ በተገባ ነበር። ዘመነ ካሴም ሆነ ሌሎቹ ፋኖዎች በሕዝቡ ስም ለትግል የተነሱ ስለሆነ፣ሕዝቡም እምነት የጣለባቸውና የሚችለውን ድጋፍ ሁሉ ስለሚሰጣቸው ሌላው ቢቀር

ከመንግሥት ጋር ለመደራደር ሲያስቡ የገንዘብና የሞራል ድጋፍ ከሚያደርግላቸው ጋር መወያዬት ይገባቸው ነበር።ገንዘቡን እንደሚሰበስቡት ሁሉ ሃሳቡንም መሰብሰብ ነበረባቸው። በስከጀርባ መደራደር ማለት የችግሩ ሰለባና ባለቤት የሆነውን ሕዝብ አያገባህም ማለት ይሆናል።ክህደትም ነው እንላለን።

በቀጣዩ በዬቦታው የሚንቀሳቀሱት ፋኖዎች ዘመነም ሆነ ሌሎቹ ታሰሩ ብለው  የተሸከሙትን መሳሪያ እንደራደር በሚል የጅል ፈሊጥ እንዳያወርዱት እናሳስባለን።የገጠማቸውን  ችግር ቢገልጹ ሌላው አገር ወዳድ ሊያሶግድላቸው ይችላል።ለአማራው ሙብት ማስከበር ያነሱትን ነፍጥ ሙብቱ ሳይከበርለት ማውረድ ትክክል ካለመሆኑም በላይ፤ዓላማ ቢስ ያደርጋል።

አውነት በአደራዳሪ ሽማግሌዎች በኩል የተደረገ ክህደት ከሆነም አደራዳሪዎቹ የካዱት ዘመን ካሴን ብቻ ሳይሆን መላ አማራውን ብሎም በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምነውን ሁሉንም ሕዝብ ነው።ይቅር የማይባልና ጊዜ የማይሽረው ወንጀል ነው።መካድ በፋኖ ዘመነ ካሴ  አልተጀመረም።ብዙ ሃቀኛ ታጋዮች ተከደዋል፣ለሞት ተዳርገዋል።

የኢትዮጵያ  ሕዝብ እንዲሁም ለሙብቱ የቆሙ ሃቀኛና ደፋር ልጆቹ በራሳቸው ዜጋ ተክደው የመከራና የስቃይ ብሎም የሞት ሰለባ መሆናቸው የዛሬ ሳይሆን  የቀደመ የታሪክ አካል ነው።በከሃዲ ዜጎቿ ተሳትፎና ተባባሪነት ኢትዮጵያ ለወራሪ ሃይሎች ተጋልጣለች፣መከራና ፍዳዋ በዝቷል።ለጣልያን ያደሩትን ባንዳዎች ብቻ ሳይሆን ከዚያም ወዲህ የነበሩትን  ሥርዓቶች ተቃውመው የተነሱትን ሃቀኛ አገር ወዳዶች አሳልፈው የሰጡ ከሃዲዎች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።አሁንም ቢሆን አብረው የመከሩትን፣ለአንድ ዓላማ የተነሱትን የቅርብ ጓደኛ አሳልፎ መስጠትና መካድ የሚሾሙበትና የሚሸለሙበት ሙያ ሆኗል። ከሃዲ ከሩቅ አይመጣም የሚባለውም ለዚያ ነው።

ወጣም ወረደም የአንድ ግለሰብ መከዳትና ከትግሉ ሜዳ መወገድ ትግሉን በመጠኑ ቢጎዳውም እስከመጨረሻው ሊያስቆመው አይችልም።በትግል ውስጥ ግለሰቦች ይሞታሉ፣ይቆስላሉ፣ከትግሉም ሊያፈነግጡና ሊከዱም ይችላሉ።ይህንን ታሳቢ ያላደረገና መፍትሔም ያላዘጋጀ ትግል ለውድቀቱ ምክንያት  የሚሆነውን ቅራቅንቦ ተሸክሞ  የሚጓዝ  ማለት ነው። በተጨማሪም ትግል ከግለሰቦች እጅና ቁጥጥር ወጥቶ በድርጅታዊ ተቋም ካልተመራ ለውድቀት የተጋለጠ ይሆናል።በግለሰቦች ዙሪያ የተሰበሰበ ጭፍራ ጨዋታ ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ ብሎ በያቅጣጫው ይበታተናል። ለዚያም ነው ደግመን ደጋግመን ሕዝባዊ ትግሉ በሕዝባዊ ድርጅት ይመራ ያልነውና አሁንም የምንለው።ጠንካራ ድርጅት ካለ የግለሰቦች መውጣትና መውረድ፣መያዝና መሞትም ቢሆን ትግሉ  እንዲዳከም ዕድል አይሰጥም። ከከሃዲዎች ጉያም ውስጥ ለመግባት አይችልም።ጠንካራ የመረጃ ሰንሰለት ስለሚኖረውም፣ ከሃዲና አድርባዮች ሰርገው በመግባት እንደልባቸው ሊርመሰመሱበት አይችሉም።

የአማራ ብልጽግና ተብዬዎቹ ህሊና ቢሶች ባርነታቸውን የሚያረጋግጡበት ቢኖር የኦነግ ኦሕዴዱ ብልጽግና  አፋኝ ቡድኖች በክልሉ ውስጥ እንደልባቸው እዬተዘዋወሩ የአማራውን ተወላጅ በተለይም የፋኖ አባላትን በግፍ እንዲጨፈጭፉ መፍቀዱ ብቻ ሳይሆን በፊት አውራሪነት ግንባር ቀደም ሚና መጫወቱ ነው።አለቃው ኦነግ ኦሕዴድ በክልሉ ውስጥ እንደልባቸው እዬተንቀሳቀሱ ኦሮሞ ያልሆነውን ኢትዮጵያዊ በተለይም የአማራውን ተወላጅ ለሚጨፈጭፉት አጋሮቹ  ድርጅታዊ ድጋፍ፣መረጃ፣ ስንቅና ትጥቅ ሲሰጣቸው እያዩ  በራሳቸው ክልል ውስጥ ቁመንለታል ብለው ለሚነግዱበት  ሕዝብ ሙብት የሚታገሉትን ፋኖዎች እያሳደዱ መግደል፣ማሰርና ትጥቅ ማስፈታት ዘመን የማይሽረው ቅሌትና ባርነት፣የሚጠዬቁበትም ወንጀል  መሆኑን ሊያውቁት ይገባል።

በፋኖ ዙሪያም መታወቅ ያለበት ቢኖር ፤-ፋኖ ማለት በጫካ ውስጥ ድምጹን አጥፍቶና ተሸሽጎ የሚቀመጥ ማለት አይደለም።የሕዝቡን ጥቃት የሚከላከልና በአጥቂዎች ላይ ሳያስቡት እርምጃ የሚወስድ ፈጥኖ ደራሽና ደም መላሽ ማለት ነው።ከተግባር ጋር ያልተሳሰረ ፋኖነት አለ ብለን አናምንም።ከብልጽግና ጎን ተሰልፎ ወያኔን መውጋት ከሆነም ከሚሊሽያና ከልዩ ሃይል ተለይቶ አይታይም። ለእኛ ፋኖ ማለት ሕዝቡን ከመከራና ከስቃይ፣ከጭፍጨፋና ከመፈናቀል የሚያድን፣ብሶት የወለደው ሕዝባዊ ወታደር ማለት ነው።አገሩንም ከውጭና ከውስጥ ጠላቶች የሚከላከል ማለት ነው። በዬክፍለሃገሩ ስም የሚንቀሳቀሱት ፋኖዎች በአንድ አገራዊ ወይም የአማራ ፋኖ ስም መጠራት ይኖርባቸዋል።ያ ካልሆነ ለጎጠኝነትና ለልዩነት በር ይከታል።ይህ በአስቸኳይ መታረምና መስተካከል አለበት እንላለን።

በመካሄድ ላይ ያለውን የሁለት አገር አጥፊ ቡድኖች ጦርነት ኢትዮጵያን በመግደልና በማዳን መካከል የሚደረግ ጦርነት አድርገው የሚያዩ ብዙዎች ናቸው።ግን አይደለም!ሁለቱም ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ናቸው።አነግ ኦሕዴድ ከመሃልና ከምዕራብ ወያኔ ከሰሜንና ከምሥራቅ ሆነው በመናበብ የሚፈጽሙት አገር የመቀራመት ሴራ ነው።ለዚያ እንዲያመቻቸው ለኢትዮጵያ ዋልታና ማገር የሆነውን የአማራውን ማህበረሰብ በጦርነት አላሽቀው፣በኤኮኖሚ አድቅቀው ፣በውስጡ አንድነት እንዳይኖረው ከፋፍለው ማዳከም የእስትራቴጅያቸው ዋና መመሪያና ስልት ነው።ይህንን እያዩና እዬሰማ በኦሕዴድ ጥላ ሥር መብቴን አስከብራለሁ ፣ፋኖን አጋልጬ በማገኘው ጥቅም ተደስቼ ከጠላቶቼ ጋር በሰላም እኖራለሁ የምትል ካለህ በሬ ካራጁ ይውላል ወይም ዶሮ ጭራጭራ መታረጃዋን አወጣች የሚለውን ተረት እንዲተርቱብህ የፈቀድክ ጅልና ጅላጅል ነህ ማለት ነው።

በብልጽግናም ሆነ በአማራ ክልል ባለሥልጣኖች በኩል የምታረጋግጠው ክብርና መብት፣አገርና ሰላም የለም።እነዚህን የምታረጋግጠው የሁሉም ቀውስ ፈጣሪ የሆነውን ወያኔንና በሥልጣን ላይ ያሉትን የብልጽግና ተብዬው የጎሰኞች ቡድንና አጫፋሪዎቻቸውን ለዘለቄታው ስታስወግድ ብቻ ነው።ለዚያም

1 - -የሕዝባዊ ትግሉ ጎራ የሚፈልገውን በቅጡ ማወቅና መረዳት አለበት፤ለዚያም የዓላማ ጥራት ያለው ድርጅት መፍጠር ይኖርበታል።ትግሉ በግለሰቦች ቁጥጥርና ፍላጎት ላይ የወደቀ መሆን የለበትም።ግለሰቦች ለድርጅት ታማኞች ይሆናሉ እንጂ ድርጅት ለግለሰቦች ታማኝ መሆን የለበትም። እንዲያ ከሆነ ለአምባገነን ሥርዓት በር ይከፍታል።

2-የተበታተነው ትግል በአንድ ድርጅታዊ መዋቅር መሰባሰብ አለበት።በጎጥና በመንደር ህሳቤ የሚመራ ከሆነ ለእርስ በርስ ንትርክና ሽኩቻ ያጋልጣል፤ለጠላት ጥቃትም አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል።

3- በውጭና በአገር ውስጥ የሚደረገው የድጋፍ እንቅስቃሴ በአንድ የጋራ አካል መመራትና መቀናጀት አለበት።ከትግሉ መሪ ድርጅትም ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል።የመደገፍ ብቻም ሳይሆን ድርጅቱ በሚከተለው የትግል ሂደት ላይ ብሎም በሚያሳልፈው ውሳኔ ላይ ሃሳብ የመሰንዘርና ድምጽ የመስጠት መብትም መኖር ድርጅቱን ጠንካራ ያደርጋል፣የደጋፊዎችን እምነት ይፈጥራል።በጠቅላላ አባላት መካከል የአሽከርና የጌታ ግንኙነት ሊኖር አይገባም።አሰላለፉ ቢለያይም ሁሉም የድርጅቱ ብሎም የትግሉ እኩል ባለቤት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

ከጠላት ሚስጥር ለመደበቅ በሚል ሽፋን አባላትን ማወቅ ከሚገባቸው ጉዳይ ማውጣት ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፤ዴሞክራሲያዊ አሠራርም አይሆንም።ድርጅታዊ አወቃቀሩና የአባላት ምልመላው በጥሩ ሁኔታ ከተሟላ ለሰርጎ ገቦች አመቺ አይሆንም።ሰርጎ ገቦች ቢኖሩ በሰርጎ ገቦች ላይ ጠንካራ እርምጃ ሊወስድ ይገባል። የሚወስደውም እርምጃ ድርጅቱንበደጋፊዎቹ የተከበረ፣በጠላቶቹ የተፈራ ያደርገዋል።

4 ጠላትና ወዳጁን ጠንቅቆ ማወቅ የትግል ሁሉ መጀመሪያ ነው።እባብ ለመደ ተብሎ በብብት ውስጥ አይያዝም።

ጽሑፋችንን የምናጠቃልለው በተደጋጋሚ በአገራችንና በሕዝባችን ብሎም በታጋዮች ላይ የሚከሰቱትን የክህደት አይነቶችና ምልክቶች ፣የሚያደርሱትንም ጉዳት በጥቂቱ በሚያሳዩ አባባሎችና ምክሮች ይሆናል።

ክህደት የተለያዩ ቢመስሉም ግን አንድ አይነት ውጤትና ትርጉም አላቸው።

ክህደት በቤተሰብ(Parental)፣በፍቅረኛ(intimate ,lover or partner)፣በድርጅት(Institutional) በሚያምኑት የዓላማ ጓደኛ(Interpersonal) በኩል ይፈጸማል።

በቤተሰብ በኩል የሚፈጸመው ክህደት ልጅን ተንከባክቦ የማሳደግን ሃላፊነት በተገቢው አለመወጣትና ሕጻናት ልጆችን ለመከራና ለአደጋ አጋልጦ መስጠት የሚያደርጉት መጥፎ ተግባር ነው።

በፍቅረኛ ወይም በትዳር ጓደኛ ላይ የሚከሰተው ክህደት ለሃብት ቅርምት ሲባል ወይም በስከጀርባ ከሌላ ጋር የሚፈጸም የፍቅር ግንኙነት ሲኖር ነው።

ድርጅታዊ ወይም ተቋማዊ ክህደት፣- አንድ ድርጅት የተቋቋመበትን ዓላማ ከግቡ ሳያደርስ በመካከሉ አፈንግጦና አቅጣጫ ቀይሮ ለሌላ ዓላማ ከተሰለፈና ፣አምነው የተከተሉትን ሁሉ ሲከዳ ማለት ነው።

ጓዳዊ ክህደት፣ይህ በሚያምኑትና ቃል በገቡት፣ለአንድ ዓላማ አብረው በተሰለፉት ጓደኛ/ጓዶች በኩል አሳልፎ በመስጠትና በማጋለጥ የሚፈጸም ክህደት ነው።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የክህደት አይነቶች በእኛ አገር ማህበረሰብአዊና ፖለቲካዊ ህይወቶች ውስጥ ሲንጸባረቁ የኖሩ፣እንግዳ ያልሆኑ የስነምግባር ግድፈቶች ናቸው።ሁሉንም አይነት ክህደቶች አስተናግደናል፤አሁንም እያስተናገድን እንገኛለን።ከሁሉም ይበልጥ ጎልቶ የሚታዬውና ብዙሃኑንና አገራችንን ይበልጥ የጎዱት ድርጅታዊና ጓዳዊ ክህደቶች ናቸው። ለአንድ ዓላማ የቆሙ ሰዎች ሳይውል ሳያድር ሌላውን ፈንግለውና አሳልፈው ሰጥተው የመጠቀሙን ብልሹ ምግባር የምናውቀው ስለሆነ ከሙብዛታቸው የተነሳ ብናነሳ ጊዜ አይበቃንም።ከመከራና ከከፉ ሥርዓት ያወጡናል ያልናቸውና ተስፋ የጣልንባቸው ድርጅቶች ሳይውል ሳያድር ቃላቸውን አጥፈውና ከደው ከጠላት ጋር መሞዳሞዳቸውን አይተናል ፤አሁንም እያዬን ነው።ስለዚህ መካድና መካካድ ለእኛ ኢትዮጵያውያን አዲስና እንግዳ ነገር አይደለም።እንደውም የሚኮሩበትና የሚሾሙበት ሙያ ሆኗል።ለዚያም ነው መስዋእት ቢከፈልም የምንፈልገውንና የምንመኘውን ሳናገኝ ለተራዘመ ችግር የተዳረግነው።

ስለክህደት የተሰጡትን የተለያዩ ምክርና ሃሳቦችን በማቅረብ የዛሬውን ቅንብራችንን እንደመድማለን።

ክህደት ከቅርብ እንጂ ከሩቅና ከጠላት በኩል አይመጣም !

ክህደት እምነትን ብቻ ሳይሆን ልብንም ይሰብራል፤ከሚያምኑትና ከሚወዱት በኩል ሲመጣ ደግሞ ይበልጥ ያማል!

ውጫዊ የአካል ቁስል ይድናል፤ክህደት የሚያመጣው የልብ ቁስል ግን የማይሽር የህይወት ዘመን ቁስል ነው!

አደገኛ ሰዎች ከድተውህ እንዳልከዱ የሚጮሁ ናቸው።አድምተውህ ደማሁ ብለው ከሚጮሁት ተጠንቀቅ!

ልትሞትለት ያልከው ሰው የምትገደልበትን ጠመንጃ ይሸከማል ወይም ከሞትህ ጀርባ ይቆማል። የሴራው አጋር መሆኑን አትዘንጋ!

ለጥቅማቸው ብለው የከዱህን ዳግም አትመናቸው!

እምነት ማጉደልና መክዳት የሰብአዊነት ደረጃን ይቀንሳል!

ክህደት የዓላማ ቢሶች ሁለእንተናዊ መግለጫ ነው!የማጥፊያ መሳሪያቸውም ነው!

ብዙ ዓመት ወስዶ የተገነባን እምነት የሰከንድ ዕድሜ ያላት ክህደት ትንደዋለች!

በአሁኑ ጊዜ ከከሃዲዎችና ከክህደት መራቅ አይቻልም፣ተመሳስለው ስለሚመጡ!

ዝምታም አንዱ ክህደት ነው!

ትንሽ ክህደት ትልቅ እምነትን ትገላለች!

በአገራችን ከቀረቡት የዘፈን ግጥሞች መካከል ስለክህደት እንዲህ ተብሏል

እንጠጣ ነበር ውሃ ባንድ ኮዳ፣

በጣም ያሳዝናል ያመኑት ሲከዳ።

ሲወዱት የጠላ ሲያምኑት የከዳ ሰው፣

ከጅን ከጂ ይከዳው ብድሩ ይድረሰው።

የወደዱትና ያመኑት ባይከዳ፣

አስቸጋሪው ዳገት ይሆን ነበር ሜዳ።

አዎ ከሃዲዎች ባይኖሩ ኖሮ ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑ የውስጥና የውጭ መንግሥታት ጉልበታቸው ቈጠማ ነበር።

ከሃዲ መንግሥታትና አጫፋሪዎቻቸው በሕዝብ ትግል ይወገዳሉ!

ኢትዮጵያ በቁርጠኛ ልጆቿ ክብሯን ትቀዳጃለች፣አንድነቷንም ታስከብራለች!!